ሳምንት 23

4ኛ ክፍል

የመገናኛ ብዙሃን አባላት ተሳትፎ

Leveled



Amharic

ይህ አጋዥ የንባብ መጽሐፍ ከዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ. (USAID) በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በሴቭ ዘ ቺልድረን (Save the Children)፣ በትምህርት ሚኒስቴር እና በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ትምህርት ቢሮ የጋራ ትብብር ተዘጋጅቶ ታተመ፡፡

2009 ዓ.ም.

The CC By license lets others distribute, adjust, and build upon this work, for free or commercially, as long as credit is given to the original creation. However, any changes from the original must be indicated.
For more info please refer: *https://creativecommons.org/licenses/*

የመገናኛ ብዙሃን አባላት ተሳትፎ

4ኛ ክፍል | ሳምንት 23 | Leveled



የመምህራን ማስታወሻ

ይህ መጽሀፍ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት መሰረት የንባብ ክሂልን ለማሳደግ እና ልጆች ጥሩ የተዘጋጀ ነው። ተማሪዎች ይህንን መጽሀፍ ተጠቅመው የመናገር፣ የማዳመጥ፣ የማንበብና የመፃፍ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ የወላጆች ና የመምህሮች እገዛና ክትትል እጅግ በጣም ወሳኝ ነው። መምህሮች፣ በመጽሀፉ ውስጥ ያሉ ይዘቶችን በተገቢ መንገድና በትክክል በማንበብና በማስነበብ ድርሻቸሁን ልታበረክቱ ይገባል። የተከበራችሁ መምህራን እና ሌሎች አጋዥ አንባቢዎች፣ ይህንን መጽሀፍ ለተማሪዎች ከማንበባችሁ በፊት በግላችሁ አንብቡና ሀሳቡን በመረዳት በቂ ዝግጅት አድርጉ።

መፅሃፉን ከማንበባችሁ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

1. ስለመገናኛ ብዙሃን ምንነት ግለፁ።
2. በትምህርትቤታችሁ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት ምን ዓይነት ተግባራት ያከናውናሉ?
3. መፅሃፉ ስለምን የሚገልፅላችሁ ይመስላችኋል? ለምን?



ምዕራፍ አንድ፡ የመገናኛ ብዙሃን አባላት ስብሰባ

በትምህርትቤቱ ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት ለአጣዳፊ ጉዳይ ተሰብስበዋል፡፡ ሰብሳቢያቸው መምህርት ምስራቅ ሰሞኑን ስለሚዘጋጀው መፅሄት ከመገናኛ ብዙኃን አባላት ጋር ለመወያየት አጀንዳውን ለአባላቱ አስተዋወቁ፡፡ አባላቱም የሚያሲይዙት ሌላ አጀንዳ ካለ እንዲናገሩ እድል ሰጧቸው፡፡ ተማሪዎቹም ስለአሰራራቸውና በሁለተኛው ወሰነትምህርት ቅድሚያ ስለሚሰጣቸው ተግባራት እንዲሁም ስለሰዓት አከባበር እንዲወያዩ አጀንዳ አስያዙ፡፡

በመጀመሪያው አጀንዳ መሠረት በየዓመቱ ስለሚዘጋጀው የትምህርትቤቱ መዕሄት መወያየት ጀመሩ። በመዕሄቱ ውስጥ ከሽፋን ጀምሮ እስከይዘቱ ድረስ ምን ምን ርዕሰ ጉዳዮች እንደሚካተቱ ተወያዩ። የክበቡ አባላትም በየተራ እየተነሱ በመዕሄቱ ውስጥ የሚካተቱ አምዶችን ገለፁ። የስፖርት፣ የሴቶች፣ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎች ተሞክሮ፣ የእንግዳና የትምህርትቤቱ አቢይ ተግባራት አምዶች እንዲካተቱ ቢደረግ ተመራጭ እንደሆነም ተስማሙ።

በመቀጠል መዕሄቱን ለማዘጋጀት አስተባባሪዎችን መረጡ። የኮሚቴ አባላቱ በቁጥር አምስት ሲሆኑ ሁለት ሴቶችና ሶስት ወንዶች ሲመረጡ መምህራቸው ወይዘሮ ምስራቅ አብረዋቸው የማስተባበር ስራ እንደሚሰሩና በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ከጎናቸው እንደሚቆሙ ገለፁላቸው። አንደኛው አጀንዳ በዚህ ሁኔታ ከተጠናቀቀ በኋላ ሁለተኛና ሶስተኛ አጀንዳዎችን በደንብ በመወያየት ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ተግባራት ለማከናወን ተስማሙ። በመቀጠል በማንኛውም ተግባር ሰዓት አክብሮ መገኘትና ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ተወያዩ። ሰዓት የማያከብሩ የክበቡ አባላት በደንባቸው መሰረት አስፈላጊውን ቅጣት ሊቀጡ እንደሚገባቸው አፅንኦት በመስጠት አሳሰቡ። በመጨረሻም የተለያዩ ማሳሰቢያዎች ከተነገሩ በኋላ ተለያዩ።

አምስቱ የመገናኛ ክበብ የኮሚቴ አባላትና አስተባባሪ መምህራቸው ወይዘሮ ምስራቅ መፅሄቱን ለማዘጋጀት የተለያዩ ፅሁፎችን በግብአትነት ለማግኘት ማስታወቂያ ለጠፉ። በማስታወቂያው መሰረት ብዙ ፅሁፎች ወደክበባቸው ይጎርፉ ጀመር። እንዲሁም አካል ጉዳተኞችንና በትምህርታቸውና በስነምግባራቸው አርአያነት ያላቸውን ተማሪዎች በማነጋገር ዘገባዎችን በመዘገብ አሰባሰቡ። አሁን የመፅሄቱን ቅርጽና ይዘት ፈር የማስያዝ ተግባር ቀርቷቸዋል። መፅሔቱን ለማዘጋጀት በቅድሚያ የሽፋን ገፅ ስዕል ምን ይሁን በሚል ተስማሙ።

የሽፋን ገፅ ሥዕሉ የትምህርትቤታቸውን ገፅታ የሚያሳይና በውስጡ አንዲት ሴትና አንድ ወንድ ተማሪ በጋራ ሆነው የደንብ ልብስ ለብሰው መሳል እንዳለበት ተስማሙ። ሁለቱ ተማሪዎች መፅሃፉን በደረታቸው ይዘው ብሩህ ተስፋን ሲያልሙ የሚያሳይ ሥእል ቢሆን እንደሚመረጥ ተስማሙ። የሽፋን ገፅ ሥዕሉን ቁጭ ብለው በመንደፍ ሃሳብ ሰጡበት። በመቀጠልም በስነፅሁፍ ክበብ የሥዕል ችሎታ ያላት ፎዚያ ሥእሉን በመሳል እንድትተባበራቸው ጠየቋት። ፎዚያም ሥእሉን በሚገባ በመሳል ለመገናኛ ብዙሃን ክበብ በስጦታ መልክ አቀረበች።



ምዕራፍ ሁለት፡ የመጽሄት ዝግጅት በመገናኛ ብዙሃን አባላት

ከሶስት ቀናት በኋላ የውስጥ ገፆችን ለማቀናበር የኮሚቴ አባላቱ እንደገና ተሰበሰቡና መወያየት ጀመሩ። የሰበሰቧቸውንም ዘገባዎችና ፅሁፎች እየመረጡ ማደራጀት ጀመሩ። ምስጋናውን፣ የይዘት ማውጫውንና መግቢያውን በጋራ እየተወያዩ ፃፏቸው። ከዚያም አምዶችን በመከፋፈል ያገኟቸውን ግብዓቶች በመጠቀም ሊፅፉ ተስማሙ። የስፖርት አምድን ዳንኤል፣ የሴቶች አምድን ሶፊያ፣ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ተማሪዎችን ተመክሮ አምድ አቤል፣ የእንግዳ አምድን አበባ፣ የዓመቱ የትምህርትቤቱን አበይት ተግባራት ደግሞ ኑረዲን እንዲፅፍ ተከፋፈሉ።

ዕሁፉን በሚያደራጁበት ጊዜ ማድረግ የሚገባቸውን መመሪያዎች በሚገባ ተወያዩ። በዕሁፉ ውስጥ አላስፈላጊ ድግግሞሽን ማስወገድ፣ ዘገባቸውም እውነተኛ፣ አጭርና ግልፅ መሆን እንደሚገባው ተወያዩ። ለዕሁፉ አጋዥ መግለጫ የሚሆኑ ፎቶግራፎች ሊኖሩ እንደሚገባና የሚመለከታቸው ሰዎች ፈቃደኝነትም መጠየቅ እንደሚገባ ተወያዩ። የእያንዳንዱ የመፅሄት አምድ በስንት ገፆች መጠናቀቅ እንዳለበትም ወሰኑ። በመጨረሻም ሁሉም የኮሚቴ አባላት የተሰጣቸውን ስራ አጠናቀው ከሳምንት በኋላ ተገናኝተው እንደሚገመግሙት ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ።

የስፖርት አምድ እንዲያዘጋጅ የደረሰው ዳንኤል ስለትምህርትቤቱ የስፖርት እንቅስቃሴ የተዘገቡትን ዘገባዎች ከስፖርት ክበብ በመሰብሰብ ማስታወሻ አዘጋጀ። በመፅሄቱ ውስጥ ስለልጃገረዶችና ስለወንዶች የእግርኳስ እንቅስቃሴ የታዩ ጉልህ ክንዋኔዎችን ፃፈ። በጠረጴዛ ኳስ፣ በመረብ ኳስ፣ በተለያዩ ሌሎች ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎችም የታዩትን አመርቂ ተግባራት በጥሩ ሁኔታ ፃፈ።

እንዲሁም በአመቱ ውስጥ በአቅራቢያቸው በሚገኙ ትምህርትቤቶች ስላደረጉት ስፖርታዊ የልምድ ልውውጥም በሚገባ ዘገበ። አስፈላጊ ፎቶግራፎችንም ከትምህርትቤቱ የመገናኛ ብዙሃንና የሥነፅሁፍ ክበቦች አሰባሰበና የፎቶግራፎቹን ባለቤቶች መልካም ፈቃደኛነት በመጠየቅ በዕሁፉ በአስፈላጊ ቦታዎች ሁሉ እንዲገቡ ማስታወሻ ያዘ። በመጨረሻም በጥሞና ድምፁን ከፍ አድርጎ ዘገባውን በደንብ አነበበውና

አንዳንድ ግድፈቶችን ለማስተካከል ሞከረ። ከዚያም ጓደኛውን ጠራና አሁንም ድምፁን ከፍ አድርጎ አነበበላት። ጓደኛውም ጥሩ ዘገባ እንደፃፈ ነገረችውና አንዳንድ ቦታ ላይ የሀሳብ ቅደምተከተል መፋለሱን አሳየችው። አንዳንድ ቃላትንም በሌሎች ቃላት እንዲተካ አማከረችው። የስርዓተነጥቦችን አጠቃቀምም በጋራ ተወያዩባቸውና እንደገና አስተካክለው ፃፏቸው።

የሴቶች አምድን የምታዘጋጀው ሶፊያ ደግሞ በትምህርትቤቱ የሚገኙ ሴት ተማሪዎችና ሴት መምህሮች ስላከናወኗቸው ተግባራት የተለያዩ ዘገባዎችን አሰባሰበች። በስርዓተፆታ ክበብ በዓመቱ ውስጥ የተከናወኑ አበይት ክንዋኔዎችን በማስታወሻዋ ላይ ፃፈች። ጎበዝ ሴት ተማሪዎችን በማነጋገር ለጉብዝናቸው መሰረት የሆኗቸውን ጉዳዮች እንዲገልፁ ቃለመጠይቅ አደረገችላቸው። እነሱም የራሳቸው፣ የቤተሰባቸውና የመምህሮቻቸው የጋራ ጥረት ለዚህ እንዳበቃቸው ገለፁላት። የሴት የእግር ኳስ ቡድን ተጠሪን (አምበልን) አነጋገረችት።

የሴቶች የእግር ኳስ ቡድን አባላት ከሌሎች ከአቻ ትምህርትቤቶች ጋር ተጫውተው ዋንጫ የወሰዱበት ዓመት ነው። ሶፊያ ለዋንጫ ያበቃቸውን ጥንካሬ እንዴት እንዳገኙ ጠየቀቻት። የቡድኗ አምበልም የቡድን አባላቱ በስነምግባር የታነጹ፣ መብትና ግዴታቸውን የሚያውቁ የሰውነት ማጎልመሻ መምህራቸውን ምክር ተግባራዊ የሚያደርጉ መሆናቸውን አብራርታ ገለፀችላት። ሶፊያ ከእግር ኳስ ቡድን አምበሏ ጋር ያደረገችውን ቃለመጠይቅ በሥርዓት አደራጅታ ፃፈችና ምስሎች

የት ጋር እንደሚካተቱ ምልክት በማድርግ የስፖርት አምድ የፅሁፍ ዝግጅቷን አጠናቃ ፃፈች፡፡

አቤል ደግሞ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎች ተመክሮ አምድ ለመፃፍ ተማሪዎቹን አነጋገረ፡፡ በአመቱ ውስጥ ያሳዩትንም ተመክሮ ከየክበባቱ እየሰበሰበ ዘገበ፡፡ አንዳንዶቹ የተለያዩ ስነፅሁፎችን በመፃፍ ተሰጥኦዋቸውን ያሳዩ ናቸው፡፡ ልቦለዶችን በመፃፍ፣ ግጥሞችን በመግጠም፣ አጫጭር ጭውውቶችንና ድራማዎችን በማቅረብ የታወቁ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ የእንስሳትን ድምፆች አስመስለው የሚሉ ናቸው፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የተለያዩ ቅርፃቅርፆችን የሚሰሩ፣ በፈጠራ ስራዎች ላይ የተካኑ ናቸው፡፡

አቤል የእያንዳንዳቸውን ተሞክሮ በሚገባ እየተመለከተ ዘገበ፡፡ በተለይ በእግሩ ላይ ጉዳት የደረሰበት ብርሃኑ የሰራውን ናሙና ሄሊኮፕተር በማድነቅ ሄሊኮፕተሩን ለመስራት ያነሳሳውን ሁነት እንዲያጫውተው ጠየቀው፡፡ ብርሃኑም በልጅነቱ አባቱ ጋራዥ ሲሰሩ አብሯቸው እየሄደ ይመለከት እንደነበር ገለፀለት፡፡ እንዲሁም በቴሌቭዥንና በሬዲዮ በሚተላለፉ የልጆች ክፍለጊዜ ላይ ብዙ ልጆች የፈጠራ ስራቸውን ሲያቀርቡ ሲያስተውልና ሲከታተል እንደነበር ነገረው፡፡ ሄሊኮፕተሯ በዲናሞ እንደምትንቀሳቀስም እየሞከረ አሳየው፡፡ አቤል ልጁን በማድነቅ የሰራውን ተግባርም በዓመታዊ መፅሄቱ ላይ እንዲሚያካትተው ገልፆለት ተሰነባበቱ፡፡



ምዕራፍ ሶስት፡ ልዩ ተሰጥዎ ያላቸው ተማሪዎች ተሞክሮ

አቤል ወደሌሎች ልዩ ተሰጥኦ ወደአላቸው ተማሪዎች በመሄድ ተሞክሯቸውን እንዲነግሩት ጠየቃቸው። ልዩ የፈጠራ ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች መካከል አንዷ ሰላማዊት ስትሆን የውሃ ማጣሪያ በመስራት የአመቱ ተሸላሚ ተማሪ ናት። ሰላማዊት ብዙ ወጪ ከማይጠይቁ ከተለያዩ የአካባቢ ቁሳቁሶችና እቃዎች የውሃ ማጣሪያውን እንደሰራችው ለአቤል አሳየችው። ባለመስታወት ሳህን፣ ነጭ የጎማ ኩባያ፣ ጫፍ ላይ ደግሞ የውሃ መያዣ ጎማ (ሀይላንድ) በመጠቀም በነጭ መሃሉ በተበሳ የጎማ ኩባያ ላይ ትላልቅ ጠጠሮችን፣ ትናንሽ ጠጠሮችን፣ ደቃቅ ከሰልና የታጠበ አሸዋ በቅደምተከተል አደረገች። ይህንን ጎማ ስሩ በተበሳ ነጭ የጎማ ሳህን ውስጥ በማስቀመጥና በሳህኑ ቀዳዳ የሀይላንድ ጎማን በመቀርቀር የተጣራ ውሃ ማጠራቀሚያ አዘጋጅታለች። ከዚያም

ድፍርስ ውሃ በሳህኑና በጎማው (አሸዋ፣ ጠጠርና ከሰል በያዘው) ውስጥ በማድረግ ውሃው ተጣርቶ ሲወርድ ለአቤል አሳየችው። አቤልም የአራተኛ ክፍል ተማሪ የሆነችውን ሰላማዊት ስላደረገላት ቃለመጠይቅ አመስግኖ ተለያትና ዘገባውን በሚገባ አጠናቅሮ ፃፈ።

የእንግዳ አምድን ለመፃፍ ዕድሉን ያገኘችው አበባ የአመቱን ታዋቂ የመፅሄታቸውን እንግዳ ለመምረጥ በጣም ተቸግራ ነበር። ነገርግን ከኮሚቴ አባላቱ ጋር ባደረገችው መመካከር የከባድ መኪና ሾፌር የሆነችውን የወይዘሪት መስታወትን የህይወት ታሪክ ለመዘገብ ተስማሙ። ወይዘሪት መስታወት የተወለደችው በደብረ ማርቆስ ከተማ ልዩ ስሙ አብማ በሚባል ቦታ ነበር።

ወይዘሪት መስታወት እድሜዋ ለትምህርት ሲደርስ ወላጆቿ መማር እንደሚገባት ተስማምተው ወደትምህርትቤት ላኳት። መስታወትም እጅግ ጎበዝ ተማሪ በመሆን ከክፍሉ ከ1ኛ እስከሶስተኛ በመውጣት ከክፍል ወደክፍል የምትሸጋገር ነበረች። ወይዘሪት መስታወት የተለያዩ ሞተሮችን የመፍታትና የመግጠም ልዩ ተሰጥኦ ነበራት።

ስለዚህ የአስርኛ ክፍል ትምህርቷን እንደጨረሰች በቴክኒክና ሙያ መስክ ተሰማርታ ራሷን፣ ቤተሰቦቿንና ወገኖቿን ለመርዳት ጓጓች።

አበባ ሰላማዊትን ሌሎች ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጠየቀቻት፡፡ ከጥያቄዎቹ መካከል አንዱ “ለአሁኑ ስራሽ መሰረት የሆኑሽ እነማን ነበሩ?” የሚል ሲሆን ሰላማዊትም መሰረቷ እናቷ እንደሆኑ ገለፀችላት፡፡ እናቷ በጣም ጎበዝ የማስተዋል ችሎታ ስለነበራቸው ልጃቸውን ሰላማዊትንም ዘወትር ያስረዷት እንደነበር ገለፀችላት፡፡ የመኪና መንዳት ፍቅርም ያደረባት ከዚያ ቀን ጀምሮ እንደሆነ ገለፀችላት፡፡ አበባም ይህንን ህልሟን ለማሳካት የቴክኒክና ሙያ ስልጠና ከወሰደች በኋላ የከባድ መኪና ሾፌር ለመሆን የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት ልምምዷን ቀጠለች፡፡

ከዚያም የመንጃ ፈቃዷን ካወጣች በኋላ በከባድ መኪና ሾፌርነት ተቀጠረች፡፡ ሰላማዊት መኪና በማሽከርከር የስድስት ዓመት ልምድ አላት፡፡ በእነዚህ ጊዜያት ውስጥ አንድም ቀን በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት አድርሳ አታውቅም፡፡ ሁልጊዜም መኪና ስታሽከረክር ተጠንቅቃና የትራፊክ ህግንም ጠብቃ ነው፡፡ ሰላማዊት ከሾፌርነት ባሻገር በመኪና መገጣጠም ሙያ በዲግሪ ተመርቃ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ተመርቃለች፡፡ በጉዞዋ ወቅት አንዳንድ ጊዜ የመኪና ብልሽት ቢገጥማትም ብልሽቱን ራሷ በመመርመርና በመጠገን አስተካክላ የመንዳት ብቃት አላት፡፡

አበባ የሰላማዊትን ተሞክሮ በዘገባዋ ላይ በማስፈር እንግዳ በሚለው አምድ ስር በቃለመጠይቅ አቀራረብ ስልት ለማቅረብ ፈለገች፡፡ አበባ የሰላማዊትን የህይወት ተሞክሮ በሚገባ አቀናብራ ፃፈችና መልሳ አነበበችው፡፡ መስተካከል የሚገባውን ካስተካከለች በኋላ

የሌሎች ጓደኞቿን የአፃፃፍ ስልት በማየት እንደገና አቀናበረችው። ሁሉም የኮሚቴ አባላቱ የተሰጣቸውን የአምድ ዝግጅት አጠናቅቀው በቀጠሯቸው ቀን ተገናኙ። አስተባባሪ መምህራቸው ወይዘሮ ምስራቅም በእለቱ ተገኝተው የተማሪዎቹን የመፅሄት ዝግጅት ሂደት በጋራ ገመገሙ። ተማሪዎቹ ያዘጋጇቸውን ፅሁፎች በየተራ ካነበቡ በኋላ ፅሁፎቹ እየተገመገሙ፣ መስተካከል የሚገባቸው እየተስተካከሉ እንደገና ወጥ በሆነ መልኩ መፅሄቱ ተዘጋጀ። ከዚህ በኋላ የቀረው ተግባር የመፅሄቱን ረቂቅ ለህትመት ክፍል መስጠት ነበር።

የትምህርትቤቱ ርእሰመምህርና የአስተዳደር ኮሚቴ አባላቱ መፅሄቱን እንዲያሳትሙ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት ጠየቁ። ርእሰመምህሩም በእቅዳቸው መሰረት መፅሄቱን ማሳተም ብዙም እንደማይከብዳቸው ከገለፁ በኋላ "በቅድሚያ ግን የስነፅሁፍ ክበብ ተጠሪና የአማርኛ ቋንቋ መምህሮች መፅሄቱን ቢያዩትና አስተያየት ቢሰጡበት ይመረጣል" በማለት አሳሰቡ። ወይዘሮ ምስራቅም የርእሰመምህሩን ሃሳብ በመደገፍ መጽሄቱ ቢገመገምና አዎንታዊ አስተያት ቢሰጥበት በጣም ደስ ይለናል" በማለት ተናገሩ።

በመቀጠልም የመፅሄቱን ቅጂ በማቅረብ የኮሚቴ አባላቱና የቋንቋ መምህሮቹ ሙያዊ አስተያየት ሰጡበት። ከዚያም አንዳንድ ማሻሻያዎች ተደርገው መፅሄቱ ለህትመት ቀረበ። መፅሄቱ በጣም ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ ተዘጋጅቶ የመገናኛ ብዙሃን አባላት ተረከቡና ለትምህርትቤቱ ማህበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ተሸጠ።

ምዕራፍ አራት፡ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት የትምህርትቤት እንቅስቃሴ

የመገናኛ ብዙሃን አባላት በዓመቱ ውስጥ ከሰሯቸው አመርቂ ተግባራት አንዱ የመፅሄት ዝግጅት ቢሆንም ሌሎችንም ተግባራት በሚገባ ሁኔታ አከናውነዋል። ለምሳሌ በየቀኑ የተለያዩ ትምህርታዊና አዝናኝ ፅሁፎችን በማቅረብ በሰንደቅ ዓላማ ሥነስርዓት ላይ ያነባሉ። ለተለያዩ ክበብ አባላት የስራ እንቅስቃሴ ቅስቀሳ ያደርጋሉ። ሌሎች ክበቦችንም በማገዝ ሥራቸው የተቀላጠፈ እንዲሆን ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ።

ለምሳሌ የስነፅሁፍ ክበብ አባላት የሚፅፏቸውን ፅሁፎች በተለያዩ መድረኮች ላይ እንዲያቀርቡ ሁኔታዎችን ያመቻቹላቸዋል። የአካባቢ ጥበቃ ክበብ አባላት የትምህርትቤቱን ግቢ ሲያፀዱ የክበቡ አባላት በሙዚቃና በአንዳንድ ጭውውቶች መንፈሳቸውን እንዲያድሱ

ያበረታቷቸዋል። የጤናና የፀረኤድስ ክበብ አባላትን የስራ እንቅስቃሴዎች በማስተዋወቅ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ። ከዚህም ባሻገር ለትምህርትቤቱ የማህበረሰብ አባላትና ለአካባቢው ማህበረሰብ የማስተዋወቅ ስራ ይሰራሉ።

የትምህርትቤቱ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት እነዚህን ተግባራት ሲያከናውኑ አስር ወራትን አስቆጠሩ። አሁን የትምህርትቤት መዝጊያ ቀን ደርሷል። የመገናኛ ብዙሃን አባላቱ በወላጆች ቀንም ብዙ ተግባራትን ሲያከናውኑ ውለዋል። ለወላጆችና ለትምህርትቤቱ ማህበረሰብ የትምህርትቤቱን በጎ ገጽታ አስተዋውቀዋል። በመድረክ ላይ ለሚቀርቡ የመርሃግብሩ የመክፈቻ ሥርዓቱን በማስተዋወቅና በማቅረብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል። መርሃግብሩ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሌሎችንም የማስታወቂያ ስራዎችን ሲያከናውኑ ቆይተዋል።

የክበቡ አስተባባሪ መምህርት ምስራቅ በዚህ ቀን ከመቼውም ጊዜ በላይ ስራ በዝቶባቸዋል። ሌሎቹም የክበቡ አባላት እንደዚሁ በሰራው ተወጥረው ውለዋል። በመጨረሻም የወላጆች ቀን በጥሩ ሁኔታ ተከብሮ የመገናኛ ብዙሃን አባላትም በስራቸው ሲደሰቱ አመሹ። ዓመቱን በሙሉ ሲደክሙበት የከረሙት ተግባር በጥሩ ሁኔታ መጠናቀቁ እጅግ አስደሰታቸው። ይህንን ደስታቸውን በጋራ ለማጣጣም ዝግጅት ማድረግ እንዳለባቸው ተስማሙ። ዝግጅቱን የሚያስተባብሩ ሶስት የኮሚቴ አባላትን መረጡ።

ምዕራፍ አምስት፡ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት የደስታ ቀን

ዛሬ እለቱ እሁድ ነው። የመገናኛ ብዙሃን አባላት ደስታቸውን ለመግለፅ፣ አብሮነታቸውን ለማጠናከር ባዘጋጁት ዝግጅት ላይ ተገኝተዋል። ተማሪዎቹ ዳቦ አስደፍተዋል፤ ለስላሳ መጠጦችን ገዛዝተው አቅርበዋል። ቤቱ ጨፌ ተጎዝጉዞ የሰንደሉና የእጣኑ ጢስ አካባቢውን በጥሩ መዓዛ አውዶታል። የክበቡ አባላት በሙሉ የባህል ልብሶቻቸውን ለብሰው አምረው ደምቀዋል።

የትምህርትቤቱ መምህሮችና ርዕሰ መምህሮች እንዲሁም ሌሎች ሰራተኞች በጥሪው መሰረት ሰዓታቸውን አክብረው ተገኝተዋል። በመርሃግብሩ መሠረት የዝግጅቱን ሥርዓት የከፈቱት መምህርት ምስራቅ ናቸው። ወይዘሮ ምስራቅ ክበቡ በዓመቱ ውስጥ ያከናወናቸውን ተግባራት፣ ያጋጠሙትን ችግሮች እንዲሁም በሚቀጥለው ዓመት ያቀደውን ዕቅድ ባጭሩ አነበቡ። ጉልህ አስተዋፅዖ ላበረከቱ ተማሪዎችም የምስክር ወረቀትና ሽልማት ተበረከተላቸው። በዚህ ዓይነት እለቱን በጥሩ ሁኔታ አሳልፈው ለሚቀጥለው ዓመት በሰላም እንዲገናኙ ተመኝተው ተለያዩ።

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።

1. የትምህርትቤቱ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት ለአጣዳፊ ጉዳይ የተሰበሰቡት ለምንድን ነበር?

2. የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላቱ የመወያያ አጀንዳዎች ምን ምን ነበሩ?

3. በመጽሄቱ ውስጥ የሚካተቱ አምዶች ምን ምን ነበሩ?

4. እነዚህን አምዶች ለመጻፍ ምን ምን ቅድመ ተግባራትን አከናወኑ?

5. የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላቱ በወላጆች ቀን ያከናወኗቸው ተግባራት ምንድን ናቸው?

6. በእናንተ ትምህርትቤት የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባላት ምን ምን ተግባራትን ይፈጽማሉ?

7. እናንተስ የመገናኛ ብዙሃን ክበብ አባል ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?